ነገረ ማርያም

# ክብረ ድንግል

ክብረ ድንግል ቃል በቃል ሲፈታ የድንግል ክብር ማለት ነው ። በነገረ ማርያም ትምህርታችን ከሌሎች ቅዱሳን በተለየ አካባበር ልዩ ትኩረት የምንሰጠው የድንግል ማርያምን ክብር ነው ። የድንግል ማርያም ክብር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው በምሳሌም ያለምሳሌም በትንቢት ሰዘክር የቆየ ነው ። ብሉይም ሐዲስም ሰምና ወርቅ ሆነው የድንግል ክብሯን ኅኅንነቷን ሲመሰክሩ ኖረዋል ። የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ይህን ተገንዝበው በየድርሳናቸው የድንግል ክብሯ ከሌሎች ቅዱሳን ከፍያለ የተለየ ደረጃ እንዳለው ሳያሳስቡ ያለፉበት ጊዜ የለም በተለይም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዘወትር በሚነበበው የተአምረ ማርያም መቅድም እንደተገለጸው ለድንግል ማርያም ተገቢ የሆነ የጸጋ ስገድ ሊቀርብላት እንደሚገባ በዝርዝር ከነምክንያቱ አስረድቷል ። ነቢያት በትንቢታቸው ፡ ሐዋርያት በስብከታቸው ሊቃውንት በትርጓሜያቸው ቀዊብረው ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል የጸጋ ክብር ምስጋና ማቅረብ ተገቢና አስፈላጊ መሆኑን ስላስረዱን ድንግልን ማክበራችን በልማድ ሳይሆን ምሥጢሩ ገብቶን በክርስቲያናዊ ሕይወት ታንፀን በውነት ክብርት ነሽ በእውነት ቅድስት ነሽ በእውነት ቡርክት ነሽ እያልን ልናወድሳት ልናከብራት ይገባናል ።

በተአምረ ማርያም በዘወትር መቅድም ሊቁ ቅ ዮሐንስ አፈወርቅ ያመሰግነውም ምስጋና እንደሚከተለው ይነበባል ። ንባቡን ከነምስጢሩ ለማስተዋል ያብቃን አሜን ።

“ለእመቤታችን ስግደት እንዲገባ (የጸጋ ስገድ ማለት ነው)

ሦስት ጊዜ እሰግድልሻለሁ ። እግዚአብሔር ካንቺ ሰው ሆኖ ሙሽራ ከጫጉላው እንዲወጣ ካንቺ የወጣ እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ (ብሎ ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ እንዳመሰገነሽ አመሰግንሻለሁ ።) የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው ባገኘውም ጊዜ የተሸከመው እውነተኛ ቸር ጠባቂያችን ክርስቶስ ካንቺ የተወለደ እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ። እግዚአብሔር በደይን የጣላት የሔዋን ዕዳ የሚኃዳ ማሠሪያዋ ባንች የተቆረጠላት እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ። እግዚአብሔር በብሩህ ደመና ተጭኖ መጥቶ በማኅፀንሽ ያደረ እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ።

“በቅዱሳን ነቢያት በቅዱሳን መላእክት አድሮ የሚኖር ካንቺ ተወልዶ የተገለጸልን እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ። ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምንሰግድለት ቃል የሚባል እግዚአብሐር ባንቺ ባሕርይ ካንቺ ይወለድ ዘንድ የወደደሽ እመቤቴ ማርያም ደስ ይበልሽ ።

“እኔ ለምእመናን ወንጌልን የማስተምርለት የጌታ እናቱ እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ። ከወለድሽው በኋላ ማኅተመ ድንግልናሽ እንዳይለወጥ አድርጎ የጠበቀሽን አማኑኤልን የወለድሽው እመቤቴ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ። ማኅተመ ድንግልናሽ ሳይለወጥ ንጉሥ ክርስቶስን የወለድሽው እመቤቴ ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ። ማኅተመ ድንግልናሽ ሳይለወጥ ንጉሥ ክርስቶስን የወለድሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ልዩ መድኃኒታችንን በመውለድሽ እናትን አገልጋይን ተብለሻልና ።

“እግዚአብሔር ፀሐርይሽን ባሕርይ አድርጎ ባለሟልነትን አግኝተሻልና እመቤቴ ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል ።

እኛ ተምንወደው እሱም ከሚወደን ልጅሽ ኃጢአታችንን ያስተስርይልን ዘንድ ለምኝልን ።” በመዝሙረ ዳዊት ክብረ ድንግል በትንቢት “ኵሉ ክብራ ለወለተ ንጉሥ ሐሴቦን በዘአዝፋረ ወርቅ ዑጹፍት ወሑብርት” (መዝ. ፵፬ ቁ ፲፫) ተብሎ ተነግሯል ። በምሥጢር አፈታት ሳይሆን ገጸ ንባቡን ላይ ላዩን ስንመለከተው በሰም አነጋገር ስለምድራዊት ንግሥት (እቴጌ) ክብርና ሞገስ የሚናገር ይመስላል ። ውስጣዊ ወርቃዊ ትርጉሙ ግን ስለ ምድራዊት እቴጌ ሳይሆን ስለ ሰማያዊት ንግሥት ስለ ቅድስት ማርያም ክብር ጸጋ የተነገረ ትንቢታዊ ኃይለ ቃል ነው ። በቅዳሴያችን “ ተውህቦ ምሕረት ለሚካኤል ወብሥራት ለገብርኤል ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል ” እንላለን ። ፍቹም “ምሕረት (ርኅራኄ) ለሚካኤል ተሰጠው የምሥራች መናገር ባለምሥራች መሆን ለገብሬኤል ተሰጠው ለድንግል ማርያም ሰማያዊ ሀብት ሰማያዊ ጸጋ (ክብር) ተሰጣት ” ማለት ነው ። በዚሁ መሠረት የዳዊትን ቃል ከላይ የጠቀስነውን ገጸ ንባቡን እንዳለ በአማርኛ ስንፈታው “ ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብርዋ ነው ። ልብሷ የወርቅ መጎናጸፊያ ነው ” ተብሎ ይነበባል በሌላም አነጋገር አማርኛው ሲቃና ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ለእቴጌ ሁሉ ክብሯ ነው ። ማለት ብስጡ ብስያጡ ምንጣፉ ወርቅ ባለ መርገፉ ፤ ወርቀ ዘቦ ግምጃ ደርባ ደራርባ ለለበሰች ለእቴጌ” ይባላል ። የዚህ ንባብ ምሥጢራዊ ትርጓሜው በቀጥታ ድንግል ማርያምን ይመለከታል የንጉሥ ልጅ የተባለችው እመቤታችን ናት ። በሥጋዊ ልደት በአባቷ በቅዱስ ኢያቄም በኩል የትውልድ ሐረጓ ወደላይ ሲቆጠር ከንጉሡ ከዳዊት ትወለዳለች። ስለዚህም ነው ወንጌላዊው ማቴዎስ የጌታን የትውልድ ሐረግ ሲቆጥር “መጽሐፈ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም” “የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ ” (ማቴ. ፩ ቁ. ፩) ብሎ ክርስቶስ የሥጋ ትውልዱ ከዳዊት መሆኑን የጻፈው። ወንጌላዊው የዕብራውያንን የአጻጻፍ ስልት ልማዳቸውን ላለመለወጥና ምክንያት ለማሳጣት የጌታን ልደት በዮሴፍ በኩል ቢቆጥርም ዝቅ ብሎ ክርስቶስ ከድንግል ያለ አባት መፀነሱን መወለዱን ዕንስ

ላም ልደቷም በመንፈስ ቅዱስ ግብር የተከናወነ መሆኑን ስላስረዳን በዮሴፍ አንጻር የድንግል ማርያም የትውልድ ሐረግ እንደተቆጠረ ግልጽና የማያ ጠራጥር ሆኖልናል ። የቅዱስ ወንጌል ዘርፍ ሆነውን ነገረ ማርያም የተባ ለውን መጽሐፍ ብንመለከት ከዮሴፍ በኩል ሳይሆን በድንግል ማርያም በኩል ቆጥሮ እናገኘዋለን ። በማቴዎስ ወንጌል ምዕ ፩ቁ፲፭ ላይ የተጠቀሰው አልዓዛር የዘር ግንድ መሆኑ ነው መገናኛው ግንዱን አል ዓዛርን መሠረት አድርገን ስንቆጥር በማያሻማ ሁኔታ የአምላክ እናት የእመቤታችን ትውልዷ በቀጥታ በአ ባቷ በኩል ከንጉሥ ዳዊት ወገን መሆኑን ያረጋግጥልናል ። ከዚህ የሚ ከተለውን አቆጣጠር ትንመልከት - አቆጣጠሩም የማቴዎስ ወንጌልንና የነገረ ማርያምን መጽሐፍ በማዛ መድ የትውልድ ሐረጓ ሲቆጠር የሚ ያሳይ ነው ።

ከአብርሃም . . . ዳዊት . . . አልዓዛር

(ማቴ ፩፥፪ -- ፲፭)

አልዓዛር — ማታን — ያዕቆብ — ዮሴፍ

(ማቴ ፩ ፡ ፲፭ — ፲፮)

አልዓዛር—ቅስራ— ኢያቄም - ድንግል ማርያም (ነገረ ማርያም)

በሰንጠረዡ እንዳሳየነው መገናኛው ግንዱ አልዓዛር ሆኖ አልዓዛር ማታ ንና ቅስራን ይወልዳል ። ማታን ያዕቆ ብን ፣ ያዕቆብ የድንግልን ጠባቂ ዮሴ ፍን ይወልዳል ቅስራ ኢያቄምን፤ ኢያቄም ድንግል ማርያምን ይወል ዳል ። የንጉሡ የዳዊት ልጅ ስለሆነች የሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ተባለች ።

ወደ ጀመርነው ትርጓሜ ስንመ ለስ ከላይ ያወሳነው ግጸ ንባብ እንደ ሚከተለው ይፈታል ። ለንጉሥ ልጅ ለመቤታችን ክብሯ ሐሴቦን ዘእምሐሴ ቦን ነው ይህም ማለት ክብሯ አፍአዊ ምድራዊ ሥጋዊ ያይደለ ውሥጣዊ ሰማያዊ መንፈሳዊ ነው ። ልብሷ የወ ርቅ መጎናጸፊያ ነው ማለትም ወርቅ ንጽሕናዋን ሲያሳይ መጎናጸፊያው ወርቀ ዘቦው ግምጃው ደግሞ ፍጹም ክብሯን ሰማያዊ ሀብቷን ልዕልናዋን ያመለክታል ። ስለዚህም ንጽሕት ሲተረጎም ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ፣ ንጽሐ ልቦና ለያዘች ለእመቤታችን ክብሯ ውሣጣዊ ሰማያዊ መንፈሳዊ ነው አፍአዊ ምድራዊ ሥጋዊ አይደ ለም ተብሎ ነው ። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በዳዊት ልሣን "ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብሯ ነው" (መዝ ፵፬ ቁ፲፫) ብሎ የተናገረላትን ፍጹም ክብሯን ተመልክተን በትርጓሜ ወንጌላችን ሳይቀር ማርያም ብሂል ልዕልት ማለት ነው ። ልዕልትም ማለት ከፍ ከፍ ያለች የከበረች ክብ ሯም መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን (ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ነው) ብለን እናመሰጥራለን ክብሯ ከሥላሴ በታች ከቅዱሳን ሁሉ በላይ እንደሆነ የተገነዘበው ቅዱስ ኤፍሬም ድንግል ማርያምን ባመሰገነ በት ውዳሴው አምልቶ አስፍቶ ተና ግሮላታል አባባሉም የዳዊትን አነ ጋገር የሚያጎላ የሚተረጉም ነው ። "የዐቢ ክብራ ለማርያም እምኵሎሙ ቅዱሳን እስመ ድልወ ኮነት ለተወ ክፎ ቃለ አብ ዘይፈርህዎ መላእክት ወየአኩትዎ ትጉሃን በሰማያት ጸረቶ ማርያም ድንግል በከርሣ ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል እስመ ኮነት ታቦተ ለኡሐዱ ዘእምቅድስት ሥላሴ" ብሏል (ውዳሴ ዘረቡዕ) ትርጉም "ከቅዱሳን




ክብር የማርያም ክብር ይበልጣል የአብን ቃል ለመቀበል በተገባ ተገ ኝታለችና መላእክት የሚፈሩትን ትጉሆች በሰማያት የሚያመሰግኑትን ድንግል ማርያም በማኅፀንዋ ተሸከ መችው ይህች ከኪሩቤል ትበልጣለች ከሱራፌልም ትበልጣለች ከሦስቱ አካል ለአንዱ ማደሪያ (ታቦት) ሆናለችና" ማለት ነው ። ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም አንቀጸ ብርሃን በተባለው ድርሳኑ ድንግል ክብሯን ምስጋናዋን በማመሳጠር ጽፎላታል የኢትዮጵያ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው የአምላክ እናት ምሥጋና "ለእውነተኛ ፈራጅ ለእግዚ ኣብ እናት ምስጋናና አገልግሎት ይገባ ታል ። ቅድስት ሆይ ብዕዕት ነሽ የተ መሰገንሽና የተባረክሽ ነሽ የከበርሽና ከፍ ከፍ ያልሽ ነሽ የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል ነሽ አምላክን የወ ለድሽ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ ከተለዩ የተለየሽ የመለኮት ማደ ሪያ ነሽ ። ከፍጥረት ሁሉ ይልቅ የተከበ ርሽ ሆይ አብ የወደደሽ ወልድ ያደረብሽ መንፈስ ቅዱስ ያረፈብሽ (የጸለለብሽ) ተባልሽ ። በምድር ላይ ከፍተኛ አርያ ምን የሆንሽ ከሰማያት በላይ ያለ የአ ርያም የልዑል ሰፍራ ምትክ አንቺ ነሽ ። ቅዱሳን ነቢያት ካህናትና ነገሥ ታት ያንቺ ምሳሌ አድርገው በውስጧ የኪዳን ሕግ ጽላት ያለባት ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለየችውን ሰሩ ቅድስት ሆይ ልጅሽ ይቅርታውን ያድ ለን ዘንድ ለምኝልን ።" ብሏል ።

እስካሁን ከቅዱሳን ሊቃውንት ትርጓሜ ያየነው ሐተታ የድንግልን ክብር የሚመሰክር ስለ ገናናነቷ የሚ ናገር ምስጋናዋን የሚያበስር ሆኖ አግኝተነዋል ። ከዚህ ቀጥለን አልፎ አልፎ በነቢያት አፍ የተነገረውን በብሉይ ዘመን ያለውን ስለ ክብረ ድንግል የሚያመለክተውን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጥቅሶች እናገናዝባለን።

ሀ' መኃ ፬ ቁ ፯ "ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ምንም ምን ነውር የለብሽም"

ለ' መኃ ፮ ቁ ፱ ና ፲ "ርግቤ አንዲት ናት መደምደሚያዬም አንዲት ናት ። ለወለደቻት የተመረ ጠች ናት ። ልጆችም ባዩአት ጊዜ አመሰገኑአት ። ንግሥታትና ዕቁ ባትም ምስጋና ሰጡአት ይህች

ማንናት? እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጎበኝ እንደጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሐይ የጠራች እንደ ክቢም ጦር የምታስፈራ''

ሐ/ ትንቢተ ኢሳይያስ ፵፱፥፳፪ና ፳፫ "ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እነሆ እጄን ወደ አህዛብ አነሣለሁ ። አላማዬንም ወደ ወገኖቹ አቆማለሁ ወንዶች ልጆችሽንም በብብታቸው ይመጡአቸዋል ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ተሸክመው ያመጡአቸዋል ነገሥታትም አሳዳጊዎች አባቶችሽ ይሆናሉ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ ። ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል። የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ እኔም እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቂያለሽ እኔን በመተማመን የሚጠባበቁ አያፍሩም ።''

መ/ ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ. ፷ ቁ ፲፬ "የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤልም ቅድስት የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል ።''

መንፈሳዊ ጥበብ የተሰጠው ጥበበኛው ሰሎሞን መኃልየ መኃልይ በተባለው መጽሐፉ እጅግ ጥልቅ የሆነውን መንፈሳዊ ትምህርት እውነተኛ መዋደድ ባላቸው በሙሽራና ሙሽሪት መስሎ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን ስለ እግዚአብሔርና ስለእስራኤል ስለ ድንግል ማርያምና ስለ መንግሥተ ሰማያት በምሳሌያዊ አቀራረብ ሰም ለበስ በሚባለው አነጋገር ያቀርብልናል ። እኛ በዚህ ጽሑፋችን የምናተኩረው ስለ ድንግል ማርያም ክብር የሚያወሳውን ብቻ ስለሆነ ተመልካቾች የጽሑፉን አካሄድ በመገንዘብ እንድታስተውሉ ስናሳስባችሁ የምሥጢራት ባለቤት ጥበቡን ዕውቀቱን ለሁላችንም እንዲገልጽልን ከመማፀን ጋር ነው ።

ቢቅዳሴያችን "ተውህበ ልቡና ለዳዊት ወጥበብ ለሰሎሞን'' ልቡና ለዳዊት ተሰጠው ጥበብም ለሰሎሞን ማለታችን በነገሥት ቀዳማዊ ምዕ ፫ ቁ. ፯—፲፪ ሰሎሞን በጸሎት ጠይቆ ጥበብን ከፈጣሪ በማግኘቱ ነውና እኛም እሱን አርአያ በማድረግ የሐዋርያው የያዕቆብን ምክር እዝናት ገንዘብ በማድረግ መንፈሳዊ ጥበብ እንዲከሰትልን ያለ ነፍገት የሚለግሰውን አምላካችንን መለመን መማፀን ምን ጊዜም አስፈላጊና ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑን እንዘንጋ (ያዕ. ፩ ቁ ፭—፰) "ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ምንም ምን ነውርም የለብሽም'' (መኃ. ፬ ቁ ፯) ይላል ።

በትንቢታዊ መነጽሩ ተመልክቷት ድንግልን ወዳጄ ሆይ ይላታል ቅዱሳን ሁሉ የሚወዷት በሁሉ ዘንድ የተወደደች ሁሉ ተስፋ የሚያደርጓት ሁሉም ወዳጃችን ማርያም እያሉ የሚያፈቅሩዋት እንደሆነች ለማስገንዘብ ፈልጎ ወዳጄ ሆይ አላት ። ሁለንተናሽ ውብ ነው ምንም ምን ነውርም የለብሽም ማለቱም ለጊዜው ድንግል ማርያም መልክ ከደም ግባት የተከናወነላት እንደሆነች ሲያስረዳ ፍጻሜው ግን በንጽሕና በድንግልና የተዋበች በነፍስ በሥጋ በውስጥ በአፍአ የተቀደሰች ከመርገም ከኃጢአት ሁሉ የነጻች ንጽሐ ሥጋ ፣ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ያላት ከአዳምና ከሔዋን መርገምና ኃጢአት የተለየች ምንም ዓይነት ነውር እድፍ የሌለባት በአጠቃላይ ንጽሕት ቅድስት መሆኗን ይገልጻል ። ይኸም አባባል መንፈስ ቅዱስ በመልአከ መበስር በቅዱርስ ገብርኤልና በነቢይት ኤልሳቤጥ አድሮ "ቡርክት አንቲ እምአንስት'' አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ (ሉቃ ፩ ቁ ፳፰ና ፵፪) ብሎ ከአናገረላት የምስጋናና የክብር ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው። እኛም ይኽን መሠረት በማድረግ እንደ አባቶቻችን ሊቃውንት የእነርሱን ፈለግ አርአያ ተከትለን እንደአቅማችን ቡርክት ነሽ ክብርትነሽ ሁለንተናሽ በድንግልና በንጽሕና የተዋበ የአማረ ነው ምንም ምን ነውረ ኃጢአት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የለብሽም የክርስቲያን ወዳጅ የሁሉ ፍቅረኛ ማርያም ቅድስት ነሽ ክብርት ነሽ እያልን እናመሰግናታለን እናከብራታለን ።

ቀጥሎም በመኃልየ መኃልይ ምዕ ፮ ቁ ፱ና ፲ ላይ የተጠቀሰውን እንመርምር ። ሰሎሞን "ርግቤ አንዲት ናት መደምደሚያዬም አንዲት ናት'' ይላል ። ርግቤ የተባለችው በርግብ የተመሰለችው ድንግል ማርያም ናት ርግብ ቂም በቀል የሌለባት የዋሂት ገር እንደሆነች ድንግልም ጎዳጊተ በቀል የዋሂት ገር ርኅርኅት ናት ስለ ዚህም ርግበ ሰሎሞን ትባላለች ። ሰሎሞን ርግቤ ብሎ አመስግኗታል በርግብ መስሏታልና ። የርግብ የዋኀነት በቅዱስ ወንጌል ተረጋግጧል ጌታ ሐዋርያትን ሲልካቸው "ኩኑ የዋሃን ከመ ርግብ'' (ማቴ ፲ ቁ ፲፮) ብሏቸዋል እንደርግብ የዋሆች (ገሮች) ሁኑ ማለት ነው ።

ስለዚህ ርግብ ለደግ ነገር ሁሉ ምሳሌ ናት መንፈስ ቅዱስ በዮርዳኖስ የተገለጸው በአምሳለ ርግብ ነበር ይኸውም የሚያመለክተን በክርስቶስ የምሕረት የይቅርታ ዘመን እንደሆነ ክርስቶስ ጎዳጊ በቀል (የዋህ) ሆኖ ዓለምን ሁሉ እንደሚያስታርቅ ኃጢአታቸውንም ይቅር ብሎ በየዋህነት ምሕረትን እንደሚያድል ለማብሰር መንፈስ ቅዱስ በርግብ አርአያ መታየቱን ያሳስበናል (ሉቃ ፫ ቁ ፳፪)።

ጌታ ሐዋርያትን እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ማለቱ መንፈስ ቅዱስ የዋህ ጎዳጊ በቀል እንደሆነ እናንተም የዋሆች ቂም በቀል የሌላችሁ ሁኑ መንፈስ ቅዱስን ምሰሉት ለማለት ነው ። ዳግመኛም ክርስቶስ ራሱን አብነት እንድናደርግ እሱ የዋህ ትሑት እንደሆነ እኛም የእርሱን አርአያነት ተከትለን የዋህነትን ከእሱ በመማር የዋሆች (ገሮች) ትሑቶች እንድንሆን አስተምሮናል ። (ማቴ ምዕ ፲፩ ቁ ፳፱) እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ሲል እንደ እኔ የዋሆች ሁኑ ማለቱን እንገንዘብ ። ስለዚህ ድንግል ማርያም የዋህነትን ከመንፈስ ቅዱስ ከልጅዋ ከወዳጅዋም ከኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ ያደረገች ስለ ሆነች ይህንን አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ የተረዳው ጥበበኛው ሰሎሞን "ርግቤ አንዲት ናት መደምደሚያዬም አንዲት ናት'' ማለቱም በየዋህነት በቅድስና ከሰዎች ሁሉ በጠቅላላ ከፍጥረት ተወዳዳሪ የሌላት መሆኗን ያሳያል ። የመጀመሪያይቱም የመጨረሻይቱም ፍጽምት ርግብ መንፈሳዊት ድንግል ናት ። መንፈስ ቅዱስ በቅድስናውና በየዋህነቱ (ርኅራኄው) ተወዳዳሪ የሌለው የአብና የወልድ መንፈስ ነው ። የዋህነቱንና ቅድስናውን ለመግለጽ በርግብ አምሳል በዮርዳኖስ መታየቱ ይኸንኑ እውነት ለማስረዳት ነው ። ድንግልም በቅድስና በየ

ዋህነት መንፈስ ቅዱስን መስላዋለች። የመንፈስ ቅዱስ የዋህነት የባሕርዩ ሲሆን ለእርሷ ግን ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ከመርገምና ከኃጢአት ጠብቆ በጸጋ ይኸንን መንፈሳዊ ጠባይ መንፈሳዊ ጸጋ ሞልቷታል አጎናጽፏታልም። ሊቁ "መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እምከርሠ እማ" መንፈስ ቅዱስ " ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ከኃጢአት ከመርገም በቅድስና በንጽሕና ጠብቋታል" ማለቱ ይኸንና ይህን የመሰለውን ሁሉ ተገንዝቦ ነው ።

እመቤታችንም ምልእተ ጸጋ ምልእተ ክብር መሆኗን በቅዱስ ገብርኤል ምስጋና ብትረዳም ከቀድሞ ጀምሮ በትሕትና የኖረች መሆኗን በማስታወስ ጸሎተ እግዚእትነ ማርያም በምንለው የምስጋና አንቀጽ "ርእየ ሕመማ ለአመቱ" የባሪያይቱን ትሕትናዋን (ውርደቱን) ተመልክቷል ።" (ሉቃ ፩ ቁ ፳፰ና ቁ ፵፰) ስትል ጥልቅ ምስጋናዋን ለፈጣሪ ሰማይት ወምድር ገልጻለች ።

ማንም ሊያገኘው የማይችለውን የአምላክ እናትነት ለመቀዳጀት የበቃችውና ድንግልናን ከእናትነት አስተባብራ በመያዝ በክብረ ድንግልና ላይ ክብረ ወሊድ የተጨመረላት በፍጹም ትሕትናዋና ገርነቷ እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል

በሔዋን ምክንያት ትዕቢት ሰውን ሁሉ ከጸጋና ከክብር ባዶ አድርጎት አራቁቶት ነበር ። በድንግል ማርያም ትሕትና ግን ለዓለም ሁሉ ጸጋን ክብርን የሚያድል ክርስቶስ የዋህና ትሑት ሆኖ በእርሱ ትሕትና እኛ ፍጹም ልዕልና ፍጹም ሰማያዊ ሀብት ሰማያዊ ክብር እናገኝ ዘንድ በማኅፀነ ማርያም አድሮዋል ። ከንጹሕ ሥጋዋ ንጹሕ ሥጋን ከንጽሕት ነፍሷም ንጽሕት ነፍስን ነሥቶ አካላዊ ቃል ወልድ ሥጋና ነፍስን ተዋሕዶ በሥጋ ማርያም ተገልጿል ።

ፍጹም ትሕትናውንና ፍቅሩን አሳይቷል ። ስለዚህ በሔዋን ትዕቢት ምክንያት ተዋርዶ የነበረ የሰው ልጅች ባሕርይ በድንግል ማርያም ትሕትና ከብሯል ድንግል በትሕትናዋ ለራሷ ብቻ ከብራበት ገናበት አልቀረችም በእሷ ምክንያት ሰው ሁሉ ከክብር ወደ ክብር ከማዕረግ ወደ ማዕረግ ተሸጋገረ እንጂ ። በፍጹም ትሕትናዋ ፍጹም ክብርን ጸጋን የተጎናጸፈች ድንግል በእውነት ከክበሩ ይልቅ የከበረች ተብላ መመስገን ይገባታል ። (ዮሐ ፩ ፡ ፩ና ፲፬ ዘፍጥ ፫ ፡ ፩—፳ ፡ ፩ ጴጥ ፡ ፭ ቁ ፭ ። ምሳ ፫ ቁ. ፴፩ ፳፯ና ቆሮ ፳ ቁ ፱) ጌታችን ለሐዋርያት "እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ያለውን ቃልና ሰሎሞን በማኅልዩ ርግቤ አንዲት ናት መደምደሚያዬ አንዲት ናት ያለውን ብናገናዝብ በየዋህነት ድንግል ማርያም ከቅዱሳን መካከል የሚወዳደራት እንደሌለ ይልቁንም ቅዱሳን ሐዋርያትና መሰሎቻቸው እንደ ርግብ ሰሎሞን እንደ ድንግል የዋሆች እንዲሆኑ የዋህነትን ከእሷ እንዲማሩ የሚመከር የሚያስረዳ ሆኖ እናገኘዋለን ። "ርግቤ አንዲት ናት መደምደሚያዬ አንዲት ናት" ሲል "እመቤታችን የዋሂትን ናት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ፍጹምት ናት ልቡናዋም ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ (እንደ ቃልህ ይደረግልኝ) በማለት በማመን የጸና ነው።" ማለት ነው" ለወለደቻት የተመረጠች ናት ልጆችም ባዩአት ጊዜ አመሰገኑአት ። ነገሥታትና ዕቁባትም ምስጋና ሰጡአት ይህች ማንናት እንደማለዳ ብርሃን የምትኀበኝ እንደጨረቃ የተዋበች እንደፀሐይ የጠራች እንደ ክቢም ጦር የምታስፈራ" ይላል ። ትርጓሜውም "ለእናቷ ለሐና አንዲት ናት ለወለደቻት ለሐና የተመረጠች ናት አዋልድ (ልጆች) ምእመናን አይተው አመሰገኑዋት ሐዋርያት ሰብአ አርድእት ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስትና ተከታዮቻቸውም አመሰገኗት በ፷ቱ ማእዘን ያሉ ሁሉ ሰአሊ ለነ ቅድስት ሳይሏት አይውሉም አያድሩምና አመሰገኗት አለ እንደጨረቃ ደምቃ እንደ ፀሐይ ሞቃ በፍጹም ጸጋ አብርታ አሸብርቃ ፍጹም ክብርን ተጎናጽፋ በረድኤት ፈጥና ምእመናንን የምትኀበኛቸው በአጋንንትና በመናፍቃን ላይ ግርምት የሆነች የምታስፈራ ባለሞገስ ማናት? ጉባኤ ካህናትን ጉባዔ ነቢያትን የምትኀበኝ በጉባዔ ካህናት በጉባዔ ነቢያት የምትኀበኝ ይህች ማናት? እመቤታችን ሥራዋ በምሥጢር የሚሆን አለ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳለችና ይኸንን ምሥጢር ብሎታል "ሑረታቲሃ በምሥጢር" አካሄዷ በምሥጢር ነው ያለውን በግዕዙ መኀልየ መኀልይ የሚነበበውን የአማርኛው ስለገደፈው እንዲሟላ አውስቶነዋልና ግራ እንደማንጋባ እንተማመናለን ።

ርግብ ክፍ ብላ በሰማይ መጥቃ ለመብረር የምትችለው በሁለት ክንፎቿ ነው ። ያላት አንድ ክንፍ ብቻ ሳይሆን ሁለት ክንፎች አሏት ። ድንግልም ወደ መንግሥተ ሰማይ ያረገችበት ከዓለም ኃጢአትና መርገም ከሰይጣን ማሳት የዳነችበት በምድርም በሰማይም የከበረችበት ሁለት አክናፈ ጸጋ አላት ይኸውም በሁለት ወገን ድንግል መሆን ወይም ድንግል በክልኤ መባል ነው። በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ስለፀነሰች ከመንፈስ ቅዱስ ያገኘችው ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ የዳነችበት በክብር ያረገችበት ልዕልና ነፍስ ያገኘችበት አክናፈ ጸጋ ተሰጥቷታል ። ሰይጣን ዲያብሎስ በቀይ ዘንዶ የተመሰለው ጌታን ፀንሳ በወለደች ጊዜ በሄሮድስና በሠራዊቱ አድሮ ሲያሳድዳት ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጣት አክናፈ ድንግልና ይኸውም ንጽሕናዋ ነው ልትድን ችላለች ይህንን በማስመልከት ቅዱስ ዮሐንስ በራእየ ዮሐንስ ገልጾታል "ዘንዶውም ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ ወልድን (ልጅን) የወለደችውን ሴት አሳደዳት . ለሴቲቱም ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት" ይላል (ራእይ ፲፪ ቁ ፲፫—፲፬)

ዘንዶው ሰይጣን ነው ልጅ የተባለው እግዚአብሔር ወልድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የተሰደደችው ሴት እመቤታችን ልጅዋን ጌታችንን ይዛ በሄሮድስ መሰደዷን የሚያመለክት ነው ። ታላቁ ንሥር የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

ንሥር ወደላይ መጥቆ ከምድር ላይ የጠፋ ቅንጣት ያሕል ሥጋ ወድቃ ሲያይ እንደማትሰወረው መንፈስ ቅዱስም ሰማያዊ አምላክ ልዑለ መንበር ቢሆንም ሰው ተሠውሮ የሚሰራውን ኃጢአት ከማወቁም በላይ በትህትና ተዋርዶ ንስሐ የሚገባውን ሰውነት የሚመለከት መሆኑን ያሳያል። ለሴቲቱ የታላቁ ንሥር ክንፍ ተሰጣት ማለቱም ለድንግል ማርያም ከዲያብሎስና ከጠቀመዶቹ የምታመልጥበት አክናፈ ጸጋ ድንጋሌ ሥጋ ድንጋሌ ነፍስ ከመንፈስ ቅዱስ ተሰጣት ማለት ነው ።